ክፍል አንድ

የሰኞ ማሕሌተ ጽጌ

ነለፉ ክረምት፡- ክረምቱ አልፎ ጥሬ ተተካ። ምድርም በአበቦች ውበት አሸበረቀች። ሙሽሪትም ሙሽራዋን ልጅ ወንድሜ ወደ ተክል ቦታው ወረደ አለች።

1. *ጽጌ አስተርአየ፡-* ማርያም ሆይ ስለ ገብርኤል ሰላምታ አበባን ይዞ እጅ ከነሣሽ ሰው ዐፅም አበባ ታየ፡ ስለዚህ የድንቅ ምልክትሽ የጣዕሙ ሽታ ደስ ባሰኘኝ ጊዜ የጌታዬ እናቱ ማርያም ሆይ ስሙ የአበባ ማሕሌት ለተሰኘ ድንቅ ምልክትሽ አሸበሸባለኹ።

2. *ሰላምኪ ማርያም፡-* ማርያም ሆይ ሰላምታሽ የድንቅ ምልክት ዕንጨትን አበቀለች፡ ከሙት አፍም አበባን አወጣች። ከምስጋናውም ኹሉ ለእኔ ደስ ታሰኘኛለችና የዚህችን ጸሎት ማንበብን

ነጫጭ ከኾኑ ጥርሶችሽ የድንቅ ምልክት ወተት (ወንጌል) ይፈሳል። ከከንፈሮችሽም ያማረ የማር ወለላ (ኦሪት) ይገኛል። ፈረቃሽ ዘመነ መጸው የኾነልሽ የአበባ ወቅት ማርያም ሆይ መጥፎ ሽታዬን በአንቺ ሽቱ አሳምሪልኝ። አንደበቴንም በፍቅርሽ ጨው አጣፍጪልኝ።

9. ሥነ መላትሕኪ ማርያም፡- ማርያም ሆይ የጉንጮችሽ ውበት እንደ ሮማን አበባ አቅላላ። በልቤም ደስታን ጨመረልኝ። ከሥንዴና ከወይን ፍሬም ይልቅ የድንቅ ምልክትሽ ፍሬ በዛ። መንፈስ ቅዱስ ሽመላም የመከር ጊዜ ደረሰ እያለ በአንደበቴ ጮኸ።

10. ገነተኪ ነፍሐ፡- ማርያም ሆይ የምስጋናሽ ሽቱ በአበቡ ወገኖች አንደበት ይፈስ ዘንድ ደቡባዊ የኾነ የመልካም ሽታ ነፋስ በተክል ቦታሽ ሽው ሽው አለ። ብልኋ የእስራኤል ድንግል ማርያም ሆይ ሥዕልሽን ኪሩብ ጋርዶት

መጥራት የወደቀውን ያነሣል። ኀጢአተኛውንም ጻድቅ ያደርጋል።

6.

ሰላተ ፍቅርኪ ማርያም፡- ማርያም ሆይ የፍቅርሽ ቀን በልቡናዬ ውስጥ ነፈሰ፡ የደም ግባትሽ አበባ ጥላም በዐሳቤ ውስጥ ተወሣወዘ። ድንቅ ምልዕተሽን እና ዐዲስ የኾነ እናገራለኹ። ምስጋናሽን ከተሞሉ ከንፈሮችሽ በከንፈሬ ሞገስን አፍሺብኝ። መንፈስ ቅዱስንም

7.

ከመ ፍሕሶ ቀይሕ፡- አበባ የተሰኘሽ ማርያም ሆይ ከንፈሮችሽ ፍሕሶ እንደ ተባለ ቀይ አበባ ናቸው። ሆድሽም ሥንዴን የተዋሐደ ነው። በአበባም የታጠረ ነው። ደንግል ሆይ የሕይወቴ አበባ ነሽ። ድንቅ ምልዕት ነሽ። የሥርዐ መንግሥትም አበባ የተሰኘሺውን አንችንም የንጽሕናሽን አበባ ተቀዳጅቼ በአበባ ምስጋና አመሰግንሻለኹ።

8.

ይውሕዝ ሐሊበ ትእምርት፡- ማርያም ሆይ

አታስቸኩይ ብለሽ ፍቅርሽን ለአንዲት ሴት አስተማርሻት።

3. አለሱ ብእሲ፦ የሰማይ ንግሥት ማርያም ሆይ ወደ ገዳም የተሰማራ አንድ ሰው እንዳስለመደው ዘወትር ሰላምታሽን ሲጸልይ ወደ ምድር ወርደሽ የተወደደ የምስጋና አበባን ከአፉ ስትቀበዪ ድንቅ ምልክትሽን ያየ ኹሉ አደነቀ።

4. አእሚርየ ማርያም፦ ማርያም ሆይ የረዳ አበባን የምታፈራ የገብርኤል ሰላምታን ዘወትር እንደ ምትወጂ ዐውቄ እንደ ምሥራች ነጋሪ እንደ ገብርኤል እጅ እየነሣኹሽ የአበባ ሽቶዎችን ከአንደበቴ ትለቅሚ ዘንድ የመልካምነትሽን ድንቅ ምልክት ከእኔ ጋራ አድርጊ።

5. ኢየንፍር ቀዊመ፦ ማርያም ሆይ የአበባ ወቅት ባለቀ ጊዜ የማያልቅ ምስጋናሽን ፈጽሜ እያመሰገንኹሽ ከሥዕልሽ ፊት መቆምን አላፍርም፡ ድንቅ ምልክትሽም እንዳስረዳ ስምሽን

ለድንቅ ምልክትሽ የደስታ በዓል ወደ ሚደረግበት ቦታ ነይልኝ ድረሺልኝ::

11. ናሁ ጸገየ:- ማርያም ሆይ ቤተ ክርስቲያንን (ምእመናን) የሚያሳምር ናርዶስ የሚባል ሽቱ ድንቅ ምልክትሽ እነሆ አብበ መልካም ሽቱን ሰጠ:: ማርያም ሆይ እንደ ፌቆና እንደ ጠቦት ዋልያ እኔን እያፋጠንሽበት መርዟ ከሚገድል የአውሬው (የዲያብሎስ) አጎት ከሽነች ከጎጢአት ፊት ወደ ድጎነት ጎዳና አሸሺኝ::

12. አብኡኒ ቤተ ወይን:- ድንግል ማርያም ሆይ ድንቅ ምልክትሽና ምስጋናሽ በአንድነት ወደ ወይን ጠጅ ቤት አስገቡኝ:: የአበባሽ (የልጅሽ) አካል የሽነች ሙሽሪትም (ቤተ ክርስቲያን) መታሰቢያን ስታደርግ መጀመሪያ በሽቱ አበረቱኝ፤ ኋላም በእንኮዮች ዐሹኝ ትላለች::

13. ተንሥኢ ወንዒ:- የጎነት ወፍ ድንግል ማርያም ሆይ ከርቤና ዐልዎ ከሚባሉ የሽቱ

ተራራዎች ተነሥተሽ ነዪ፡ መስኮቶች ያሉባት
ቤተ ክርስቲያንንም ጐብኚ።
የተወደደልሽ የትንቢት ርግብ ድንቅ ምልክትሽ
ክንፍሽ ነጭ በኾነ በብር አበባ የተሸለመ ነውያ
ጎንሽም በሚያብረቀርቅ በወርቅ አበባ ያጌጠ ነው።

14.

ሆይ አበቦችን ለማየት በወደደ ጊዜ ወደ
ተክል ቦታው የገባ ሙሽራ እጅግ እንዲደሰት
ከባድ የሐዘን ሸክምን ከኃጥኣን ላይ የሚያቃልል
ደስታ የተባለ ከአንቺ ተወልዷልና
እጅግ እደሰታለኹ።

በድንቅ ምልክትሽ

15.

ከሩቅ ኹነሽ የምትመለከቺና በደብረ ምጥማቅሽ
ለኹሉ የምትታዪ የአበባ ዱር ሽመላ
ኃጥኣንን ለማዳን ከብርና ከወርቅ
ይልቅ የሚጠቅም በምድራችን

የድንቅ ምልክትሽ

ታል ጽድቅ ተሰምቷልና ደስ ይበለሽ ደስታ ይገባሻል።

በጌጋየ አዳም ወሔዋን፡- ድንግል ማርያም

16. በአዳምና በሔዋን ሱራፌ

ሆይ በደልሽ የዘጋትን

የገነትን በርዳ አበባሽ ከኾነ በቀር ማን

ከፈታት? ሆይ ከምርጥ የመለስሽ

ሔዋን ወደ

አበባ ምድር ገብታ እንደ ጥጃ ትዘላለችና ደስ ይበልሽ።

ተፈሥሒ ድንግል፡-

17. ሥላሴ ወንድን ዓታወቂ

ከቂድስት በኤፍ አንዱን የወለድሽልን

ሆይ የሙሴ ማርያም ወገኖች ጌት

ከበርን እየመታች እኅት

ምስጋናን ትናገራለች።

ተፈሥሒ ባሕታዊት፡-

18. ድንግል ማርያም ሆይ ደንግል የሌለሽ

ብቸኛዋ

ለኃጥኣን ነፍስ ይቅርታን ኹኗልና ደስ ይበልሽ።

ድንግል ማርያም ሆይ ሰማይ አንቺን ከፍ አድርጎ ያመሰግንሻል። ምድርም የማሕፀንሽን አበባ አክሊል አድርጋ በዓልን ታደርጋለች።

19. ቀስተ ደመና ማርያም፦ ምድርን በጥፋት ውሃ ስላጠፋት ለምሕረትና ለፍትሕ እግዚአብሔር የዘረጋሽ የኖኅ ድንቅ ምልክቱ የኾንሽ ቀስተ ደመና ማርያም ሆይ ሰፊውን ሰማይ በከዋክብት እናዳስጌጠው ኹሉ ስለ አንቺ ምድርን በተክሉት አበባ አንቋጠቁጣት።

20. ብኪ ተባረኩ፦ የአባት አብርሃም የዘሩና የግዘረቱ ድንቅ ምልክት የኾንሽ ድንግል ማርያም ሆይ ኤሕዛብ በአንቺ ተባርከው ተቀደሱ። ያሸበረቀ ኮከብን የወለድሽ የያዕቆብ መውጫ ፅዩ ሳቤቅ ማርያም ሆይ የድንግልናሽ አበባ በግ ስለ ይስሐቅ ቤዛ ተሰጠ።

21. በከመ ይቤ መጽሐፍ፦ መጽሐፍ እንደ ተናገረ በፈጣሪና በፍጡር መካከል ለፅረፍት

የቃል ኪዳን ድንቅ ምልክት የኾንሽ የብርሃን ቀን ለንበተ ለንበታት ድንግል ማርያም ሆይ በአበባ የተከል ቦታ ያሉ ጻድቃን በአንቺ ይደሰታሉ። ኃጥኣንም በአንቺ ከሲኦል ይወጣሉ።

22. ለመዩኪ ነቢያት፡- ድንግል ማርያም ሆይ ምስጢራትን ያዩ ነቢያት የተዘጋች የአበባ የተከል ቦታና የተቈለፈች የምሥራቅ ደጃፍን እግዚአብሔር ለዳዊት ወገን ድንቅ ምልክትን ሰጠ ብለው ሰየሙሽ። ፀንሰሽም ሕይወትን እንደ ምትወልጂ ኢሳይያስ በግልጥ ተናገረ።

23. ተኣምርኪ ማርያም፡- ድንግል ማርያም ሆይ የነቢያት አለቃ ሙሴ ያየሽ ጳጦስ አንቺ ከመለኮት ጋራ በተዋሓድሽ ጊዜ ድንቅ ምልክትሽ በኦሪት ተሰበከ። በለመለመች ቈጥቋጦ የተመሰልሽ አንቺ በቅርንጫፎችሽ አሳርፊኝ። እሳት የኾነ አበባሽም (ልጅሽ) የኀጢአቴን እሾኽ ያቃጥልልኝ።

24. በትረ አሮን ማርያም፡- የአሮን በትር ድንግል ማርያም ሆይ ሳይተክሉሽ የበቀልሽ ውሃ ሳያጠጡሽ የለመለምሽ ነሽ። ስለዚህም ቃሉ ያማረ ያሬድ ከሱራፌል ጋራ ዐጥር ይከባታል። የረዳ አበባም በመስቀል ምልክት ይከባታል እያለ ያመሰግንሻል።

25. ሥንኪ ጸጋ፡- ድንግል ማርያም ሆይ ውበትሽ በካህኑ በአሮን ልብስ ላይ አበበ። እንደ ሮማንም ወርቅን አፈራ። ድንግል ሆይ ድንቅ ምልክትሽም መካኗ ማርታ የፀነሰችው እውነተኛ ወርቅስ ከወይን ይልቅ ገድሉ የጣፈጠ ፈቅጦር ነው።

የማክሰኞ ማሕሌተ ጽጌ

ማእረረ ትንቢተ ማርያም፦-

26. የዐዲሱ የአበባ ወቅትና የረኃብ ዘመን ለውጥ የጸጋ የፍሬ ወራት የኾንሽ የኤልዳ ነቢይ ያማረ የማር ወለላ ከይሁዳ ተራሮች እና ኰረብቶች ይንጠፈጠፋል፤ ነጭ የኾነ ወተትም ይፈሳል ብሎ የተናገረው ባንቺ ታወቀ።

ዘካርያስ ርእይ፦-

27. የኾንሽ መባቻ የእውነት ብርሃን በር በየካቲት ወር ድንቅ ምልክትሽን በኵለሄ የወይራ አጥቆች መካከል ተመለከተ። በበረሓ ወድቆ በዋለ ጊዜ የፊትሽ አበባ ሕብር መብረቅ ብልጭ አለበት።

ብሥራን ታጥአን፦- የመለኮት አበባ

28. የኾንሽ አካል ድካም ከሚመካ ከጻድቅ እስጢፋ ይልቅ ድንቅ ያላንቺ በገድሉ

ምልክትሽን የሚተማመኑ ኃጥኣን ንዑዳን ክቡራን ናቸው። ሰውን ኹሉ ማዳንስ ይቅርና ነቢያት ነፍሳቸውን ከሞኑኔ ማዳን አልቻሉም።

29. ፍቅረ መኑ፦ ድንግል ማርያም ሆይ አምሳያ ከሌለሽ ከአንቺ ከአበባዋ በስተቀር ለሞት እስኪያደርሰው ድረስ እግዚአብሔርን ከሰማይ ስቦ ወደ መሬት ያወረደው የማን ፍቅር ነው። ይህንንም ዐስቦና ጠንቅቆ ለድንቅ ምልክትሽ ምስጋናን የሚያቀርብ ሰው ንዑድ ክቡር ነው።

30. ወይን ወማሕሌት፦ ድንግል ማርያም ሆይ የወይን ጠጅና መዝሙር ልቡናን ደስ ያሰኛሉ። ለተረዳው ግን ከኹለቱ ይልቅ ምስጋናሽን ደጋግሞ መናገር ያስደስታል። ሕገ ሩካቤ የሌለብሽ የክርስቶስ እናቱ ድንግል ማርያም ሆይ ነገርን አጣጥመው ድንቅ ምልክትሽን ያመሰግኑ ዘንድ ከንፈሮቼን ከጡቶችሽ አበባ ወተትን (ወንጌልን) ቅቢያቸው።

31. **ሐዋዝ በቤተ ሰታይ፦ ድንግል ማርያም** ሆይ በመጠጥ ቤት የዘፈን እና የመሰንቆ ዝማሬ ያማረ ነው። ለታወቀው ግን ከኹለቱ ይልቅ ምስጋናሽን መስማት መልካም ነው። የኀጥኣንን ጽድቅ ያስገኘሽ **ድንግል ማርያም ሆይ** ድንቅ ምልክትሽ አስደናቂ ነው። ሰውነቴም እጅግ ትረዳዋለች። ብዙውን ግን በመጻፍ መዘርዘር አልችልም።

32. **ለዘኢይሰቲ ወይን፦ ድንግል ማርያም ሆይ** ሲራክ የወይን ጠጅ የልብ ደስታ ነውና የወይን ጠጅን የማይጠጣ ሰው ሕይወቱ ምንድን ነው አለ። ከወይን ጠጅ ይልቅ የሚጣፍጥ **ድንቅ ታምርሽንና** የእይታው ውበት የሚያስደስት የፍቅርሽ ምስጋና አበባን በመናቅ የሚያቃልል መዳን የለውም።

33. **እስከ መነኑቶ ሜልኮል፦ ድንግል ማርያም** ሆይ ሜልኮል እስክትንቀው ድረስ አንቺን ያስገኘ የእስራኤል ንጉሥ **ዳዊት** በሕግ ታቦት ፊት

እንደ አሸበሸበ ድንቅ ምልክትሽንና ኩሉ እጌም ከሥዕልሽ ፊት
አሸበሸባለኹ። እንደ ቍርባን
የሚቈጠር ምስጋናሽን የሚቃልል ሰው ግን
በሰውና በመላእክት
አንደበት የተናቀ ይኹን።
በኵናተ እሳት ዘይነድድ፡- ሱራፊ የተባለ
34. መልአክ
በሚንቦገቦግ ሌጥክም የእሳት ፍላጻ የሚጠብቅሽና
ጸሓፌ ትእዛዝ መልካም ማዘሽን
ዳሽተተልሽ ሆይ ድንቅ ታምርሽን ዕንጨት
ማርያም
በመላእክት አለቃ
አደንቅ ዘንድ
እጅ የጠላቶቼን
በሚቈራርጥ
ራስ እንደ አበባ ፈጥነሽ ቀንጥሺልኝ።
ከመ ይትፌሣሕ ጻድቅ፡- የአምላክ
እናት
35. ድንግል ማርያም
ሆይ ጻድቅ ፍርድ ሲመለስ ባየ
ጊዜ ደስ እንዲለው ጠላትን በመበቀል የድንቅ
ምልክትሽን ኀይል ግለጪ። በአባቱና በእናቱ ላይ
ቃሉን ያከፋ በልጅሽ ፍርድ ይሙት በቃ
ተብሏልና አንቺንማ የሰደበ እንዴት ይድናል?

36.

የታምርሽን ሥራ ወገኖችሽ እስከ ዓይ ድረስ ገለጥሽ ከማስደነቅ አለፈ:: ያትክልት ቦታሽም (ቤተ ክርስቲያን) ሰላምና ፍቅርን ታብብ:: የወይን ቦታችንን ዕርሻ የሚያጠፉትን ጥቃቅኑን ቀበሮዎችንም ማጥመድን አፍጥኚ::

37.

ሆይ መልአኩ እንደ ነገረው የመንግሥትን ምስጢር መጠበቅ፣ ሥራ ግን በክብር መግለጽ መልካም ነው:: ቅናት ስለያዘውም ታምርሽን የሚሸሽገውን ሰው ምድር ከጥንት ዳታንን እንደዋጠችው እስከ ነፍሱ ትዋጠው::

38.

እወድሻለኹ የሚል ድንቅ ታምርሽን ግን የማይወድ ክርስቲያን ቢኖር ክርስቲያን ሳይኾን የአይሁድ ወገንና የሐሰተኛው እስጢፋ ቡቃያ ነው:: እኔ ግን በባለ መሰንቆው ልጅ

በሰሎሞን

መዝሙር የይሁዳና የሌዊ ልጅ ድንግል ሆይ ሙሽራ ሙሽሪትን እንዲወድ ውብትሽን እወደዋለኹ እላለኹ።

39. እምደቂቀ ሕዝብኪ አነ፡- ድንግል ማርያም ሆይ ከወገኖችሽ ልጆች መካከል እኔ ድኻና በደለኛ ስኾን እንደ ንጉሥ በሀብትሽ እመካለኹ። የኃጥኣንን በደል የሚያጠፋ ድንቅ ታምርሽና ኹሉን የሚመግብ የብልጽግና አበባሽ መዝገብ አለልኛና በጽድቅሽም እንደ ጻድቅ ሰው እደሰታለኹ።

40. ጼነወኒ ተሳምርኪ፡- ድንግል ማርያም ሆይ ነፋሳት በሚነፍሱበት ጊዜ ከሩቅ ጎዳና እንደ ሚሸት እንደ ገነት መልካም ሽታ ድንቅ ታምርሽ ሸተተኝ። የሽቱዎች መዐዛ የኾንሽና የተባረክሽ የቤተ መንግሥት አበባ ድንግል ማርያም ሆይ የሰሎሞንና የዳዊት አበባ ነሽ። ሀብተ ክህነት የተሰጠው የአሮን አበባን የተመሰልሽ አበባ ነሽ።

41. ተኣምረ ትፍሥሕት ማርያም፡- የተድላ የደስታ ዘመን ማርያም ሆይ የምስጋናሽ መዐዛ ምድርን እና ሰማያትን ሞላ፡፡ በአበባሽ ምስጋናሽ አሸንፍ ዘንድ ጥንካሬን አስታጥቂኝ፡፡ በምስጋናሽ አሸናፊ የኾነ ዕውቀት ያለበትን መጽሐፍና የተሰወረ መናን ይቀበላል፡፡

42. እንበለ ትሣረር ምድረ ገነት፡- የገነት ምድር ሳትፈጠር እና የአበቦች ውበት ሳይታይ ጠቃሚ ድንቅ ታምርሽ በሥላሴ ኀሊና የነበረልሽ አሸናፊዋ የአሸናፊው አምላክ እናት ድንግል ማርያም ሆይ ወገኖችሺን የሚበድለውን ሰይጣንን ታጠፊው ዘንድ ከኤርሞን አናት ተነሥተሽ ነይልኝ ድረሺልኝ፡፡

43. ጸግይየ ሣዕር፡- ድንግል ማርያም ሆይ እኔ ሣር የኾንኹ ደካማው የኪሩቤልን አንደበት ገንዘብ አድርጌ ድንቅ ታምርሺን በመናገር ባልጨረስኹ ነበር፡፡ ነገር ግን የተሸከመቺሽን ማሕፀን አመሰግናለኹ፡፡ አንቺን መድኀኒቷን

ፀንሳ ሳለች የሚዳስሷትን በሽተኞችን ኹሉ ትፈውስ ነበርና፡፡

44. ሚ ቡርክት፡- ድንግል ማርያም ሆይ ሐና አያቀም

አንቺን የፀነሰችባትና ሟች ለድኅነት አንቺን ያፈራባት የደስታ ሰዓት ምን ያህል የተባረከችና የተቀደሰች ናት፡፡ አንዲቷ ርግቤ ሆይ አንቺ የሰው ኹሉ መድኀኒትን ኹነሻልና ስለዚህ ድንቅ ታምርሽን አደንቃለኹ፡፡

45. ሰንሰትኳ መርዓ አረጊት፡- የእግዚአብሔር ድንግል ማርያም ሆይ ለቢልቴተ ለሐና ለሽማግሌው ለኢያቀምም ሆይ የሐና አበባ ድንግል ሰሎሞን

ወገኖች ጕርምስና የታደሰብሽ መፀነሽ ጫጕላ ሰርግ ነው፡፡ አንቺን የጸጋ ፍሬ ብሎ የሰየመሽ ወይኖች አበቡ፤ትርንጎዎችም መልካም ሽታን አቀረቡ ብሎ የአበባ ምስጋናን እንዲያመሰግኑ ትንቢት ተናገረልሽ፡፡

46. ለንጉሠ ነገሥት ሰሎሞን፡- ድንግል ማርያም

ሆይ አንቺ መ·ሸራዋ ከትንቢት አንበሳ ጕድጓዱ ብቅ ባልሽ ጊዜ የንጉሦች ንጉሥ የኾነ የሰሎ·ሞን ልብ እንደ ተደሰተ ኹሉ ድንቅ ታምርሺን በሚናገሩ በደስተኞች ማኅበር መካከል የሐና አበባ ደንግል ሆይ እዘምርልሻለኹ። የደስታ መንገድንም አስተውላለኹ።

47. *ተፈሥሐት ምድር፡-* ወደር የሌለሽ የሕይወት ምልክት ድንግል ማርያም ሆይ በለሶች (ኢያቄም እና ሐና) አንቺን ለጋዋን ቀንበጥ ባቈጠቈጡ ጊዜ ምድር ተደሰተች። ሰማይም ደስ ተሰኘ። የሞት መልክተኛ እስኪፈራ ድረስ ሰይጣንም እስኪደነግጥ ድረስ የመወለድሽ ዜና ነጐድጓድ እስከ ሲኦል ደረስ ተሰማ።

48. *ዜና ልደትኪ ማርያም፡-* ድንግል ማርያም ሆይ በኤፍራታ የሰማኹትን የመወለድሽን ዜና አኹን መንታ በኾኑ በበረሓ ዛፎች ውስጥ አገኘኹት። ማርያም ሆይ እኔን ደካማውን

በኹለት ጡቶቿ ወተት እና በውስጧ ባሉ በድንቅ ታምርሽ የሽቱ መዐዛ ታሳድገኝ ዘንድ ወደ እናትሽ ቤት አስገቢኝ፡፡

49. ትመስል እምኪ ማርያም፡- ድንግል ማርያም ሆይ እናትሽ ሐና አበባን ያስገኘች ዕለተ ሠሉስን እና የምታበራ የዓለም ፀሓይን ያስገኘች ዕለተ ረቡዕን ትመስላለች፡፡ ዳግመኛም በሰማይና በምድር ዕረፍት የኾንሽ የነጻነት ምልክት አንቺን ሰንበትን ወልዳለችና ሰባትኛዋን ቀን ዕለተ ቀዳሚትን ትመስላለች፡፡

50. አይኑ ዘተገብረ ፈውስ፡- ድንግል ማርያም ሆይ ከቤተ ክህነትና ከቤተ መንግሥት ዘር ሳትወለጂ የተደረገ ድኅነት ምንድን ነው? የአበባሽ የክርስቶስ ደምም የዓለም መድኀኒትን ኾነ፡፡ ዮሐንስም በሆድ ኹኖ ለልጅሽ እንደ ሰገደ በሥጋና በነፍስ ጕልበት ለድንቅ ታምርሽ እሰግዳለኹ፡፡



ክፍል ኹለት

የረቡዕ ማሕሌተ ጽጌ

51. *ከመ ሰዶም እምኮነ፡-* ኀጢአተኞችን ወደ ንሥሓ እንጅ ጻድቃንን ልጠራ *አልመጣኹም* ብሎ የተናገረ መድኀኒታችንን የወለድሽ *የድንቅ ታምር በትር ማርያም ሆይ እግዚአብሔር* አንቺን ባያተርፍልን ኖሮ እንደ ሰዶም በኾንን ነበር። ገሞራንም በመሰልን ነበር።

52. *እመ ተሰቅለ ቈልቍሊተ፡-* ድንግል ማርያም ሆይ ቍልቍሊት ቢሰቀል በራሱም ቢተከል ያለረዳትነትሽ ድንግል ሆይ ስድስቱ ቃላትን በመፈጸም ብቻ ነፍሱን ማዳን የሚችል የለም። ድንቅ ታምርሽ እንዲደነቅ ከአንቺ ጋራ እንድመላለስ በአበባሽ የተክል ቦታ ሹሚኝ።

53. *ከመ ታቦት ሰርገት፡-* በንጽሐ ሥጋ በንጽሐ ነፍስ ያጌጥሽ በዐረብና በተርሴስ ወርቅ

እንደ ታቦት የተለበጥሽ የሸቱ ተክሎች ኢያቄምና ሐና በሦስት ዓመት ከወለዱሽ ጀምሮ ድንግል ማርያም ሆይ በቤተ መቅደስ ድንቅ የተኣምር መቀመጥን አሳየሽ።

54. ዖፍኒ ረከበት ላቲ ቤተ፡- ድንግል ማርያም ሆይ ወፍ መኖሪያ ቤት አገኘች እያልሽ በዳዊትና በቆሬ መዝሙር አመሰግንሻለኹ። ማርያም ሆይ የዝማሬ ሕግን የምታብብ በበየጊዜዋ ፍሬን የምታፈራ በውሃ ዳር የተተከለች ዕንጨትን ትመስላለች።

55. የሐዝነኒ ማርያም፡- ድንግል ማርያም ሆይ የሐናን ጡት እየጠባሽ ወደ ቤተ መቅደስ በገባሽ ጊዜ ያገኘሽ ደካም ያሳዝነኛል። ዳግመኛም ደመናን የሚረግጥ ፋኑኤል ከባለንጀሮቹ ጋራ እንደ አባት ኹኖ መናን እየመገበሽ በቅድስና የማደግሽ ምልክት ያስደስተኛል።

56. ኢጸመውኪ ወኢፈተልኪ፡- የዐዲስ ዘመን

ምልክት አበባ የኾንሽ ማርያም ሆይ፣ መንፈስ ቅዱስ የሸመነው የንጽሕና ልብስ አለሽና የጌጥ ልብሶችን ለመልበስ ፈትለሽ አልደከምሽም:: ከውበትሽስ የተነሣ እንደ ትንሽ አበባ ውበት በክብሩ ኹሉ ንጉሥ ሰሎሞን አለበሰም::

57. እምገነተ መጽሐፍ እቀሥም፡- ድንግል ማርያም ሆይ ንብ ማርን ለመሥራት አበባን እንደ ሚቃዋ ድንቅ ታምርሽን ለመናገር ከመጽሐፍ የአትክልት ቦታ እቃዋለኹ:: በጫማሽ ውሻውን ውሃ ያጠጣሽው መልካሚቱ ርግብ ማርያም ሆይ ጭንቅ በኾነ የውሃ ጥም ጊዜ ከሮማንሽ ታጠጪኝ ዘንድ ራሪልኝ::

58. ከመ ጽጌ ረዳ በምድር፡- ድንግል ማርያም ሆይ በምድር እንደ ረዳ አበባ ከመልካም ሽታና ከቅላት ጋራ በሰማይም እንደ ፀሓይ ከሙቀትና ከብርሃን ጋራ ልይሽ፤ ዘወትርም ላግኝሽ:: ርኅራኄን የተሞሉ ዐይኖችሽም ሽቱ ወደ ሚቀዳበት የድንቅ ታምርሽ ምንጭ ይጥቀሱኝ::

59. ገበ ይቀውም ፀሓይ፡- የገሊላ አበባ ድንግል ማርያም ሆይ ነቢይቱ ሳቤላ ዐይኖቿን ወደ ሰማይ ከፍ አድርጋ ፀሓይ በወርቅ ቀለበት መካከል ኾኖ ወደ ቆመበት ቦታ ከጨረቃ ይልቅ የሚያበራ ሕፃንን ታቅፋ በትንሽ ቄንጆ አምሳል ድንቅ ታምርሽን ተመለከተች።

60. እግዚአብሔር ነጸረ፡- ድንግል ማርያም ሆይ እግዚአብሔር ዓለሙን ኹሉ ተመለከተ። እንዳንቺ ያለ እናትን ግን አላገኘም። እሱን ካንቺ የተወለደውን አበባም ዳዊት አስቀድሞ ንጉሥ ያማረ ንጽሕናሽን ወዷልና ልጄ ሆይ ሰሚ ተመልከቺም ብሎ አመልክቶልሻል።

61. ስብሓተ ፍቅርኪ ማርያም፡- ድንግል ማርያም ሆይ የፍቅርሽ ምስጋና በኹሉ አንደበት ያፈራል። ድርቅንም አይፈራም። ጌዴዎን ግምጃ በዘረጋበት ቦታ አወራርዱን የተመለከተው ደረቁን የሚያረጥብ ባሕሩንም የሚያደርቅ የተአምር ልምላሜ አለሽና።

62. ፈትለ ወርቅ ወፈትለ ሜላት፡- የእውነተኛ ፀሓይ በር የኾንሽ የብርሃን ምልክት ማርያም ሆይ የወርቅና የግምጃ ፈትል የመለኮትን እና የትስብእትን ምሳሌ ሳያጎድሉ በጣቶችሽ በተስማሙ ጊዜ ፊቱ ደስተኛ የኾነ የገብርኤልን ቃልና ድምፅ በመስማት ያላባት ዐማኑኤልን ወለድሺው።

63. ዐቢይ ውእቱ ስብሓተ ተኣምር፡- ድንግል ማርያም ሆይ በድንግልና የመውለደሽ ታምር ምስጋና ታላቅ ነው። በንጽሕናም ወርቃማ ከኾነ ከሱራፌ ማዕጠንትና ቢረሌ የተባለ ዕንቁ ከኾነ ከኪሩብ ጽዋ ጋራ የሚያለመልም የአምልኮ ቍርባንን ማፍራትሽም ዕፁብ ነው። ያላንቺም ወደ ላይ የሚያርግ ጸሎትና ልመና የለም።

64. ኦ ዘ መንክር፡- ድንግል ማርያም ሆይ በአንቺ አምላል የትንቢት ኮከብ ያለበት የተሣለ ሕፃን መልክ ታምርሽን ሊገልጥ ስለታየ ይህ ድንቅ ምን ነው። ሰብአ ሰገልንም ልጅሽ በበረት

ተኝቶ ወዳበለበት ስፍራ ከሩቅ ቦታ መራቸው።

65. *እንዘ ተሐቅፊዮ ለሕፃንኪ፡-* መልካሚቱ ርግቤ ድንግል ማርያም ሆይ የኣምርና የንጽሕና ቀን በኾነ በአርባኛው ቀን ነጭና ቀይ አበባ የኾነ ሕፃንሽን ታቅፈሽ ወደ ቤተ መቅደስ እንደ ገለገልሽ ኹሉ ከልቅሶ ታረጋጊኝ ዘንድ ደስተኛ ከኾነ ከገብኤልና እንደ አንቺ ርኅሩኅ ከኾነ ከሚካኤል ጋራ ነይልኝ።

66. *ሶበ ይገነኪ አርዌ፡-* ልጅሽን ሊበላ ያሰበ አውሬ ሄሮድስ በተከተለሽ ጊዜ ወደ በረሓ በምትበሪበትና ሽሽትን በምታፋጥኝበት ገንዘብ ዮሐንስ እንዳበቀለ ክንፎችን ያበቀልሽና ፀሓይን የተጐናጸፍሽ የሰማይ እመቤት ማርያም ሆይ የተመለከተው ታምርሽን ዮሐንስ ጻፈ።

67. *ተአምረ ማፍዕኪ ለአርእዮ፡-* ድንግል ማርያም ሆይ የግፍሽን ታምር ለማሳየት ሰይጣናዊ ከኾነ ከሄሮድስ ፊት በሽሽሽ ጊዜ

ለስላሳ ከኾነ ከልጅሽ እግር ጋራ መንገድን በመኼድ የደከሙ እግሮችሽ የቆሙባትን ስሟ ቍስቋም የተባለች የተቀደሰች የገዳምሽን ምድር ደርሼ እጅ በመንሣት ልስማት በወደድኹ ነበር፡፡

68. *አፈወ ሮማን ማርያም፡-* ቀናንሞ እና አበሜ የተባሉ የሽቱ ተክል አበባ የኾንሽ የሮማን ሽቱ ድንግል ማርያም ሆይ የፊትሽ ወዝ እስኪጠወልግ ድረስ በድካምሽ ጊዜ የደረሰብሽን የልቅሶና የስደት ታምርሽን እንደ እኅትሽ እንደ ሰሎሜ መሳተፍን በተመኘኹ ነበር፡፡ መጨረሻ የሌለው ደስታሽንም በተሳተፍኹ እመኝ ነበር፡፡

69. *የበስኩ አንሰ ተክለ ቤትኪ፡-* ድንግል ማርያም ሆይ አንቺ የቤተ መንግሥት አበባ በረኅብና በጥም እንደ ደረቅሽ ኹሉ እኔ የቤትሽ ተክል በኀጢአት የነፋስ ሐሩር ደረቅኹ፡፡ ስለዚህ በእንባሽ ፈንጥቂብኝ ጩርቃው አብቦ በሚያፈራበት በታምርሽ አዝመራ ጽድቅን አጥግቢኝ፡፡

70. *ኀጋድያነ ቍስቋም ለእንስሳ፡-* የቍስቋም መንገደኞች በመንገድ የተጫኗቸውን የፈረስና የበቅሎ እግራቸውን የበረከት ቅባትን ለመቅባት ያላቃለልሽ የምሕረት ታምር ሙሽራዋ *ድንግል ማርያም ሆይ* የአበባሽን ቅባት ቅቢኝ። መልካሚቱ *ድንግል ማርያም ሆይ* ለሰው ብቻ ሳይሽን ለፍጥረት ኹሉ አዛኝ ነሽና።

71. *አመ አተውኪ ውስተ ታቦት፡- ክንፍሽ መስቀል* የኾነልሽ *የቍስቋም ርግብ ማርያም ሆይ* ከለመለመ ከወይራ ቅጠል ጋራ ወደ መርከብ በገባሽ ጊዜ የይቅርታን ዘመን *ለኖኅ* እንዳበሠርሺው የሚያበራ አበባን በመያዝ ጽድቅን አብሥሪኝ። ሃሌ ሉያ ከጥፋት መሸገሪያ ፋሲካዬም አንቺ ነሽ።

72. *እመ ብዙኃን ድንግል፡- ድንግል ማርያም ሆይ* የልጅሽን ታምር የፈለጉ ብዙዎች ቢኾኑም አመስግነው አልጨረሱም። *በሜሮን* የታተመች የልጅሽ ቤተ መቅደስ ውዴ የደረቁ *የዮሴፍ*

በትሮችን ተክሎ ወዳለመለመበት ቦታ በታናሽቱ ወርዶ ሽቱዎችን ከልብሱ አፈሰሰ አለች፡፡

73. ስፍነ ድንግል፡- ድንግል ማርም ሆይ የልጅሽን ታምራቶች ስንት ጊዜ እናገራለኹ፡፡ በአረጋዊ ዮሴፍ እቅፍ በተቀመጠ ጊዜ ትሕትናውንስ ስንት ጊዜ ዐስባለኹ፡፡ በዮሐንስ ዘንድ አዘንብሎ እንደ ቆመ ነውን ወይስ በደብረ ታቦር ብርሃኑ ብልጭ ብሎ ነጸብራቁ ሰማዮችን እንዳለበሰ ነውን?

74. በላዕሌኪ ወበዮርዳኖስ፡- ድንግል ማርያም ሆይ ጭማሬና ጕድለት የሌለበትን ሦስትነቱን ይገልጥ ዘንድ ልጅሽ ባንቺ፣ በዮርዳኖስና በደብረ ታቦር ላይ ታምሩን ሦስት ጊዜ ገለጠ፡፡ በብርሃኑም ጨለማውን አበራ፡፡

75. እምትእምርተ ሞቱ ለጽጌኪ፡- ድንግል ማርያም ሆይ ከልጅሽ የሞት ምልክት

የተነሣ ዓለም ጨለማን ከተጋረደ በኋላ ሥጋው ወደ ተቀበረበት በልቅሶ ገስግሰሽ ብርሃንን ተጐናጽፎ ባየሺው ጊዜ ልጄ በእውነት ተነሣኽን አልሺው፡፡ በአፍሽም ቍርባን የኾነ አፉን ሳምሺው፡፡



የኀሙስ ማሕሌተ ጽጌ

76. እስፍንተ ነፍሳተ ሰብእ፡- ድንግል ማርም ሆይ የታምርሽ ኀይል መዋጥ መሰልቀጥ ከለመዱ ከሲኦልና ከሞት አፍ ስንቶችን የሰው ነፍሳት ነጠቀ እያለ አባትሽ ዳዊት የትንሣኤ መሰንቆን ደረደረ፡፡ ልጅሽ የብረት ደጃፎችን እና የብረት ቍልፎችን ሰባብሯልና፡፡

77. ለጽጌኪ ማርያም፡- ድንግል ማርያም ሆይ ብላሽ ነገርን የሚናገር ሰው የልጅሽን ምልክቱን፣ በድንግልና መወለዱን እና ወደ ሰማይ ማረጉን

ይረዳ ዘንድ ከሙታን ተለይቶ መነሣቱን ባያምን እየጊዜው ወደ መቃብሩ ገብቶ የሰማይ ብርሃን መውረዱን ይይ፡፡

78. ጽጌ ደመና ማርያም፡- የደመና አበባ ማርያም ሆይ ሥጋሽን የለበሰ ወልድ የማሸነፍ ምልክት የኾነ ምርኮን ከችግር ምድር ይዞ ወደ ሽቱ ኮረብታና ወደ ሽቱ ተራራ (ወደ ሰማይ) በወጣ ጊዜ ለንጉሦች ንጉሥ የመኳንንትን በር ክፈቱ የሚል የቀንደ መለከት ድምፅ ተሰማ፡፡

79. መዐዛ ጥዑም ዘኤርምያስ፡- ድንግል ማርም ሆይ መሥዋዕት ኾኖ የቀረበ ጥሩ የኤርምያስ መዓዛ የኾነ የሆድሽ አበባ ልጅሽ በድንቅ ታምር ሽታ ባሳረገሽ ጊዜ መብረቅን የታጠቁ መላእክት በምስጋና ተቀበሉሽ፡፡ ከእነሱም አንቺን ንግሥቷን ወደ ብርሃን ድንኳን እስኪያገቡሽ ድረስ ከበሮን የሚመታ አለ፡፡ እንዚራንም የሚነፋ አለ፡

80. እግዚአብሔር ጽጌ ትንቢት፡- ድንግል ማርም ሆይ የትንቢት አበባ እግዚአብሔር የእኛ ሥጋ የኾነ ሥጋሽን ለብሶ በምድር ፊጽሞ በተገልጠን ጊዜ የባሕርያችን መመኪያ እያልን እናመሰግንሻለን፡ ዛሬም ለእናታችን ለማርያም በሰማይ የደስታ መገለጥ ተደረገ እንላለን።

81. በብሔር በኀበ ፈለስኩ፡- ድንግል ማርያም ሆይ ሰፈሬን ትቼ በተሰደድኩበት ቦታ የአርባው ቀን ምስጋናሽ መዝሙርን ኾነልኝ። ድንቅ ታምርሽ እንደ ተናገረ የመቃብርሽ ቦታ ጌቴሴማኒ መርከብን ብትኾን የእሳት ባሕርን ታሻግሪኝ ዘንድ ውደጂ።

82. አመ ነሥኡኪ እምኤደም፡- ድንግል ማርያም ሆይ የምስጋና መላእክት በእየነገዳቸው በብርሃን ክንፎቻቸው እንደ ጋሻ ጋርደው ከገነት ኾነው በተቀበሉሽ ጊዜ ከፍልሰትሽ የክብር እይታ ግርማ የተነሣ ዕርገቷ ከአበባ በረሓ የኾነላት ይህች ማን ናት ይላሉ። ስሂን እንደ

ሚባል የሸቱ ጢስ ምሰሶም ማዕጠንቷ ይሸታል ይላሉ።

83. እንዘ ይጸውረኪ በሐቂፍ፡- ለአፍንጫ መልካም ሽታ ያለሽ የገነት ዕንጨት አበባ ማርያም ሆይ ወልድ በመታቀፍ ተሸክሞ በአፉ እየላመ በቀኙ ለማሳረፍ ባሳረገሽ ጊዜ መላእክት ክንፍ በክንፍ እየተማቱ ለአቀባበልሽ ወረዱ።

84. ትእምርተ ፍልሰትኪ እምድረ ጽጌ፡- በ'ሹለት በኩል ድንግል የኾንሽ ማርያም ሆይ ከአበባ ምድር የማረግሽ ታምር በሰማይ ደመና ላይ የሐዋርያትን ጉባኤ አሳየ። ለእኛስ በጥሪ መለከት ጨ'ኸትንም በለማን ጊዜ ትንሣኤ ዘጉባኤ የደረሰ መሰለን እስኪሉ ድረስ የሞቱትን ከመቃብር ውስጥ አስነሣ።

85. ሰዊተ ሥርናዩ ለታዴምስ፡- በቀኝ እጁ በተከለሸ ጊዜ የበርተሎሜምስ ወይኑ የታዴምስ የሥንዴው እሸት የኾንሽ የጴጥሮስ የጥላው ሀብት

የጳውሎስም የመጠምጠሚያው ሀብት ድንግል ማርያም ሆይ ባንቺ ሙታን ሕያዋን ኾኑ። ሐዋርያትም በሰማይ መላእክትን ዳኙ።

86. ጽጌኪ ማርያም፡- ድንግል ማርያም ሆይ ልጅሽ ምግብንና ልብስን ኾነኝ። በቍስሉ ውስጥም መልካም መዐዛ ያለውን ሽቱ አግኝቶ ከእጄ ሽቱ ፈሰሰ እያለ ቶማስ ጎኑን በዳሰሰ ጊዜ ከሐዘን መረጋጊያ የሚኾን ድንቅ ታምርሽን ሰጠኝ።

87. ክበበ ጌራ ወርቅ ጽሩይ፡- ከሚያበራ ባሕርይ ከተባለ ዕንቍ ይልቅ እንደ ጠራ እንደ ወርቅ የራስ ቍር የአበባ አክሊል የኾንሽ ድንግል ማርያም ሆይ ለጊዮርጊስ የመንግሥቱ ሽልማት ነሽ። አንቺም ኹሉን ታሰግጂለታለሽ። እሱም ለአንቺ ይሰግዳል።

88. ጽጌ ረዳሁ ለእስጢፋኖስ፡- ከአበቦች ውበት ይልቅ የምታበሪ የእስጢፋኖስ አበባው የኾንሽ

የፊውስ ታምር ድንግል ማርያም ሆይ የሚንሿሿ ናበሊስ የተባለ ደንቢያ አንቺ ነሽ። የፊቅጦርና የአቦሊ ማኅበርተኞች የኾኑ ሰማዕታትም የለዘበ የፍቅርሽ ሿሿቴ ድምፅን በመስማት ጭንቅ የኾነ መከራን አላወቁትም።

89. ተአምረ ፍቅርኪ ማርያም፡- ድንግል ማርያም ሆይ የፍቅርሽ ታምር የሞት ጣርን አስረስቶ መራራውን አጣፍጦ ድንቅን ያደርጋል። ከአበባሽ መዐዛም (ከልጅሽ ፍቅር) የተነሣ በለማዕትነት ዐደባባይ ለሰከረ ሰው በደንቢያ መወገር ገለባን ይመስለዋል። እሳትም የቀዘቀዘ ውሃን ይመስለዋል።

90. አንብርኒ ማርያም፡- ድንግል ማርያም ሆይ እንደ ቀለበት በልብሽ ውስጥ አስቀምጪኝ። እንደ ማተብም ከፍ ባለች ክንድሽ ውስጥ ተሸከሚኝ። ንግሥት ሆይ ኑሮዬን በሕይወት አበባው ሰማዕታትን ለሸለማቸው ለሞት ፍቅርሽ ሰጥቻለኹና ስለበደሌ ግን አትናቂኝ።

91. ነገሥታት መንግሥት ሁሉ ሕግ ነው ይላል።

92. ሕገ መንግሥት ከፍተኛ ሕግ ነው።

93. ሕገ ኦሪት ሕገ ወንጌል ሕገ ቀኖና ሕገ ሲኖዶስ ሕገ ሐዋርያት ሕገ ሃይማኖት ሕገ ሥጋዌ ሕገ ጥምቀት ሕገ ቁርባን ሕገ ተክሊል ሕገ ንስሐ ሕገ ክህነት ሕገ ተአምኖ ሕገ ተዋህዶ ሕገ ፍትሐት ሕገ ቅዳሴ ሕገ ሰንበት ሕገ ጾም ሕገ ጸሎት ሕገ ምጽዋት ሕገ ስግደት ሕገ ዜማ ሕገ ቅኔ ሕገ ሊቃውንት ሕገ ሐዲስ ሕገ ብሉይ ሕገ ኦሪት ሕገ ነቢያት ሕገ ሐዋርያት ሕገ ሰማዕታት ሕገ ጻድቃን ሕገ ደናግል ሕገ ካህናት ሕገ ዲያቆናት ሕገ ቀሳውስት ሕገ ጳጳሳት

እጃቸውን ከቁረጡ በኋላ ከአንቺ አንደበትን እና እጅን አገኙ።

94. ተአምርኪ ጽጌ ሐና፡- የሐና አበባ ድንግል ማርያም ሆይ ታምርሽ በከሊሉ ፊት ባተወቀ ጊዜ በልጅሽ ትእዛዝ ወደ ሩቅ ሀገር ያደርስ ዘንድ ወፍ የመልእክቱን የደብዳቤ ብራና ይዞ በረረ። የባሕር ዓሣም ወርቅን ተሸክሞ ሐይቀኞን ይዋኛል። ጥልቁንም ይወጣል።

95. ጽጌኪ ማርያም፡- ድንግል ማርያም ሆይ ልጅሽ ታምር ማድረግን በጀመረ ጊዜ በትእዛዝሽ የጋኖችን ውሃ የወይን ጠጅ አድርጓልና ያንቺ ጎይል ምንን ማድረግ ይሳነዋል። ሥልጣንንም ማሳየትን ብትወጂስ ደንጊያውም እንጀራን በኾነ ነበር።

96. ሶበ ዐቶቦ ለማይ፡- ድንግል ማርያም ሆይ የሃይማኖት አበባ የሚኾን በገዳም የሚኖር ሳሙኤል በቅዳሴሽ እየጸለየ ውሃውን በባረከው